## ሳምንታዊ ዜና ዘገባ

ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ራዲዮ ጥር 30 ቀን 2001 ዓ.ም.

- ወያኔ የተበላሸ ፖለቲካዉን ለመጠገን ሲል አዲስ ስልት ማዉጣቱ ታወቀ በዚህም መሰረት የቴሌ ሰራተኞች በበረከት ሰምኦን የተዘጋጀዉ ሰነድ ላይ ደግፈዉ አቋም መግለጫ እንዲያወጡ ግዴታ ተጣለባቸዉ፣

- መለስ ከ4 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ አድርጎ ከ7 ሺህ በላይ ወጣቶችን በራሱ መሰብሰቢያ አዳራሽ ሰብስቦ ሲማፀን ዋለ፣

- ሁለተኛ ዲግሪያቸዉን የሚማሩ ተማሪዎች የዩኒቨርስቲ መምህር እንዲሆኑ ተገደዱ፣ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ደግሞ በግዳጅ የህክምና ባለሙያ እንዲሆኑ ወያኔ እቅድ አወጣ፣ የሚሉና ሌሎችም ይገኙበታል::

ዝርዝሩን ከሚቀጥለዉ ገፅ ጀምሮ ያንብቡ <<<>>>

የወያኔ ቡድን በደረሰበት ከፍተኛ የፖለቲካ  ኪሳራ ለማገገም ሲል ሰሞኑን አዲስ  ነው ያለውን ያረጀና ያፈጀ ስልት ጀምሮ ተግባራዊ ማድረግ መጀመሩ ታወቀ::

ለ18 ዓመታት በመሳሪያ ኃይል መንበረ ስልጣን ላይ የተቀመጡት እነመለስ ዜናዊ ከውጭ እና ከውስጥ በደረሰባቸው ከፍተኛ የፖለቲካ ኪሳራ ምክንያት ቀድሞ ህዝብን ሳያማክሩ ውሳኔ  ሰጥተው በጨረሱበት ጉዳይ ላይ  የመንግስት ሰራተኞች አቋዋም ወስደው በግዴታ እንዲደግፉላቸው የሚያስገድድ አዲስ ስልት መጀመራቸው ታውቆዋል::

ባለፈው ሳምንት ውስጥ በሺህዎች የሚቆጠሩ የቲሌኮሙኒኬሽን ሠራተኞችን በተለያዩ አዳራሾች በተለያዩ የኮርፖሬሽኑ ባለስልጣናት በሶስት ዋና ዋና ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት አድርገው ውሳኔ እንዲያስተላልፉ ማድረጋቸውን የገለፀው የደረሰን ዘገባ ውይይቱ በግዳጅ የአቋዋም መግለጫ በማውጣት እንዲጠናቀቅ መደረጉን የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

ለግማሽ ቀን ያህል የፈጀው ይኸው ውይይት አበይት ናቸው ባሉዋቸው ጉዳዮች ላይ  እራሳቸው አስቀድመው በጨረሱት ዙሪያ ያተኮረ ሲሆን ፅሁፉን ያዘጋጀው  በረከት ስምኦን መሆኑ ታውቁዋል:: አጀንዳዎቹ 1ኛ- ህልውናችንን የሚፈታተኑ በመሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ላይ ያወጣነው ህግ አግባብነት ያለው መሆኑን፤ 2ኛ-ጦሩ በሱማሊያ የፈጸመው ተልእኮ አግባብ ያለው መሆኑን እንዲሁም ለሁለት ዓመታት ሊቆይ የቻለው አክራሪ የሶማሊያን ቡድን ለማሽመድመድ እንደነበረና ይህም በተሳካ ሁኔታ መጠናቀቁን  እናም የወሰድናቸው እርምጃዎች በሙሉ ትክክል መሆናቸውን በአቋዋማችሁ በግዳጅ ደግፉን የሚል መሆኑን ዘገባው አብራርቶዋል::

በዚህም መሰረት የቲሌ ሰራተኞች በሙሉ ለግማሽ ቀን ስራ ፈትተው በዚሁ አጀንዳ ላይ ተጠምደው ውለዋል::  ወያኔ ከመቼውም ጊዜ በላይ ሙሉ በሙሉ በደረሰበት ከፍተኛ የፖለቲካ ኪሳራ ምክንያት አገግምበታለሁ ብሎ ተራና ለማንም በማይመስል መልኩ የጀመረው አዲስ ስልት ተብዬ ከድጡ ወደ ማጡ የሚከትተው እንጂ ከገባበት የፖለቲካ  ችግር የሚያወጣው እንዳልሆነ የገለፀው  ዘገባ በድርጊቱ በርካታ ሰራተኞች ተናደው የስብሰባ አዳራሹን ለቀው እስከ መውጣት መድረሳቸውንም ጨምሮ አስረድቶዋል::

የወያኔ ቡድን በደረሰበት የፖለቲካ ሽንፈትና ውርደት ምክንያት ወጣቱን ደጋፊና አባል ለማድረግ ከፍተኛ እሩጫ ላይ መሆኑን ድርጊቱ እየገለፀ መሆኑን የደረሰን

ዘገባ ገለፀ:: የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ከመላ ሀገሪቱ እንደተውጣጡ እና እንደመጡ ከተነገረ ወጣቶች ጋር ውይይት ማድረጉም ታውቆዋል::

ወያኔ የሀገሪቱን ሀብትና ንብረት መጠቀሚያ አድርጎ እየተንቀሳቀሰ ሲሆን፤ ሰሞኑን ከመላ ሀገሪቱ የተውጣጡ ናቸው የተባሉ 7 ሺህ ወጣቶችን ሰብስቦ በጠቅላይ ሚኒስትሩ መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ሲማፀን መዋሉን የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

ለ7 ሺህ ወጣቶች ለእያንዳንዱ ከምግብ ፤ከመኝታ እና ከትራንስፖርት ውጭ በቀን አንድ መቶ ብር አበል በእጃቸው እየተሰጣቸው የከረሙ መሆኑንና የወያኔን ፖለቲካ ይጠግናሉ በሚል ከተለያዩ አካባቢዎች በካድሬዎች አማካኝነት ተመልምለው ከመጡበት እስከ ተመለሱበት እለት ድረስ ከ4 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ መድረጉን ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል::

-ስብሰባው በቲሊቪዥን እንዲተላለፍ ከተወሰነ እና ዝግጅቱ ከተጠናቀቀ በሁዋላ እንዲቀር መደረጉ መለስ ለወጣቶቹ የሚያደርገው ተማፅኖ ህዝብ እንዳያውቀውና ሲማፀን እንዳያየው ከመሆኑም በተጨማሪ ከስር ያሉት ካድሬዎች ተስፋ እንዳይቆርጡ ለማድረግ ታስቦ መሆኑን ዘገባው ጨምሮ አብራርቶዋል::

የወያኔው መሪ መለስ ዘንድሮ 7 ሺህ ወጣቶችን ሰብስቦ የተማጸነ ቢሆንም አምና ግን ከ12 ሺህ በላይ ወጣቶችን ሰብስቦ ከ6 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ አድርጎ ልክ እንደ አሁኑ ያካሄደ ቢሆንም የህዝቡ እና የወጣቱ ልብ የሸፈተ በመሆኑ ድጋፍ ሊያገኝ አልቻለም::

የወያኔው ቡድን በሚያራምደው ወልጋዳ ፖለቲካ ምክንያት በርካታ ምሁራን በየጊዜው ሀገራቸውንና ህዝባቸውን እየተው ለስደት እየተዳረጉ እንደሚገኙ በተደጋጋሚ የተገለፀ ሲሆን በዚህም ሳቢያ የህክምና እና የዩኒቨርስቲ መምህራን እጥረት ሊከሰት እንደቻለ ታውቁዋል::

ወያኔ የኮታ ማሙያ እያለ በተለያዩ ቦታዎች ዩኒቨርስቲ የከፈተ ቢሆንም ውስጣዊ አደረጃጀታቸው ባዶ ከመሆናቸውም በተጨማሪ ከፍተኛ የመምህራን እጥረት ስላለባቸው ሰሞኑን አዲስ መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ ማድረግ መጀመሩን የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

የሁለተኛ ዲግሪያቸውን በመማር ላይ ያሉትን በሙሉ ወደ ተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች በመምህርነት እንዲሰማሩ የሚያስገድድ መመሪያ ያወጣ ሲሆን ብዙዎቹ ስራ የጀመሩ ቢሆንም ከፊሉ አማራጭ ስላላቸው መመሪያና ትዕዛዙን ሳይቀበሉ መቅረታቸውን ዘገባው አስረድቶዋል::

በተመሳሳይ መልኩ በህክምና ሙያ ረገድም ብዙ ባለሙያዎች ሀገራቸውን እየተው ወደ ውጭ ሀገር እየተሰደዱ በመሆኑ ከፍተኛ የሀኪም እጥረት ሊከሰት

እንደቻለና  በዚህም ምክንያት ወያኔ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን የሆኑትን መልምሎ ሊያሰለጥን መሆኑ ታውቆዋል።

በፊዚክስ እና በኬሚስትሪ ትምህርቶች የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸውን መምህራኖች በአመለካከታቸው የወያኔ ደጋፊ ናቸው የተባሉት በመላ ሀገሪቱ  ካሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ተመልምለው እንዲሰለጥኑ ለማድረግ ቅድመ ዝግጅቱ መጠናቀቁን ዘገባው ገልፆዋል።

አምባገነን የአፍሪካ መሪዎች በየሀገሮቻቸው ውስጥ ያለውን ፖለቲካዊ ፤ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ሳይቀርፉ የተባበሩት አፍሪካ መንግስታት በሚል ለማቁዋቁዋም የሚያግዘን ነው ያሉትን ሁሉ ሲያነሱና ሲጥሉ መሰንበታቸው ታወቀ።

እነ መለስ ዜናዊና መሰል የአፍሪካ መሪዎች የየሀገራቸውን ህዝቦች በመሳሪያ ኃይል አፍነው የግፎች ሁሉ ግፍ እየፈጸሙ ለምዕራባውያን ታማኝ ሎሌ በመሆን የስልጣን እድሜያቸውን ከማራዘማቸውም በላይ በማሸርገዳቸውና በማጎብደዳቸው ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን የገንዘብ ጉርሻ ያገኛሉ ያሉት እኚሁ ምሁር በሚያገኙት ገንዘብም የህዝቦችን መሰረታዊ ችግር ከመቅረፍ  ይልቅ  የጦር መሳሪያ ገዝተው ህዝቡን እያስፈራሩ እና እያዋከቡ በግዴታ እያንበረከኩ የሚገዙበት ስልት ነው ሲሉም ገልፀዋል።

የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ስብሰባ አዲስ አበባ ላይ እየተደረገ  ባለበት ወቅት የወያኔ ጦር ወደ ሱማሊያ ያለ አንዳች ከልካይ ሰተት ብሎ ገብቶ የራሱን ኬላ አቁዋቁሞ የሀገሪቱን ዜጎች በፍተሻ እና በድብደባ የቁም ስቅላቸውን እያሳየ ይህንንም የአፍሪካ ሀገራት መሪዎቹ እያወቁ ትንፍሽ ያላሉት መሪ ነን ባዮቹ ሁሉም የውስጥ  ችግር ስላለበት እከክልኝ ልከክልህ በሚል መልኩ የሚጉዋዙ አምባገነኖች ናቸው ሲሉም ተችተዋል።

በተያያዘ ዜና የወያኔው ጦር አርብ ጥር 22 ቀን 2001 ዓ.ም. ወደ ሱማሊያ ዘልቆ ገብቶ ህዝቡን እያሰቃየ እንደሚገኝ አለም አቀፍ መገናኛ ብዙሀኖች እየገለፁ መሆናቸው ታወቀ።

ለሁለት ዓመታት በሱማሊያ ሲዳክር ቆይቶ ተልዕኮውን በሽንፈት  ደምድሞ የወጣው የወያኔ ጦር  ተመልሶ በጥቂት ቀናት ውስጥ ወደ ሱማሊያ ውስጥ ዘልቆ ገብቶ ቁልፍ የድንበር ኬላዎችን ከመቆጣጠሩም በተጨማሪ ዜጎቹን በፍተሻ ስም እያሰቃየ መሆኑን የዜና አውታሮቹ ዘግበዋል።

ወያኔ ጦሩን ከሱማሊያ ባስወጣ በጥቂት ቀናት ውስጥ አልሻባብ የተሰኘው አክራሪ ቡድን ባይደዋን ጨምሮ ብዙ ቦታዎችን በመቆጣጠሩ የተደናገጠው ወያኔ ጦሩን ወደ ሱማሊያ መስገባቱን ዘገባው ገልፆል::

ወያኔ ያባረረው የለዘብተኛው እስላማዊ መሪ ሼህ ሸሪፍ ሼህ አህመድ በጅቡቲ ምርጫ ላይ ተወዳዳሪ ሆኖ በመቅረቡና ለማሸነፍም እንደሚችል በተነገረበት ወቅት ወያኔ ጦሩን ወደ ሱማሊያ ማስገባቱን ቢቢሲ የተሰኘው የእንግሊዝ አለም አቀፍ የዜና ማሰራጫ የአይን እማኞቹን ዋቢ አድርጎ የዘገበ ሲሆን ምንጊዜም እውነት አውርቶ የማያውቀው የመለስ የቅርብ ታዛዥ እና ሎሌ በረከት ስምኦን «እንኳዋን ልንገባ ሀሳቡም የለን »ሲል አይን ያወጣ ምላሽ መሰጠቱ ታውቆዋል::

በመጨረሻም የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባዔን በአዲስ አበባ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ተመድበው ሲጠብቁ ከነበሩ የፌዴራል ፖሊሶች እርስ በርስ በፈጠሩት ግጭት ሶስት ሊሞቱ እንደቻለ ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል::

ረቡዕ ጥር 27 ቀን 2001 ዓ. ም ጥበቃቸውን ጨርሰው ወደ ጊዜያዊው ማረፊያቸው ወደ ሆነው የቀድሞው ስድስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ከገቡ በሀዋላ በፈጠሩት አለመግባባት አንዱ ፖሊስ ሁለቱን ከገደለ በሁዋላ እራሱን ማጥፋቱን ታወቀ::